በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
**ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ**
FEDERAL DEMOKRAASIH UMMUUNOK
FEDERAL DINKAARAH MAYBALAALAQA

| | | |
|---|---|---|
| ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸፮<br>አዲስ አበባ ነሐሴ ፲፱ ቀን ፪ሺ፲፪ | በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ<br>የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | 26to LIGGIDIH IXXIMAK. 76<br>Addis ababa 25to dirri 2009 |

| **Mawqa** | **ማውጫ** |
|---|---|
| Gamdaado raymitte,daddos,miraaciinu kee antifiqiyya kukta gali 12,733 | የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 12733 |

**Kukti ixxima 1223/2020 I. L.L**

## Gandaado raymitteh miraaciinih antafaqiyya

dariifa qassinow kee gino gaddih selliimiya dacrisak mango roori kee gadda dacrisak; lee kee gadda libdoosaanam kee laqnah axmaamiyyi gaazitte aynukusuk baaxo yabqureenimih ligdo daccarsimak yamaate horal akah tabisan innaa kee tuhullih dorbaa kee saqi gaddih daddoosih taama, bica le caalat ginaanam faxximteemeh sabbatah

buqreh xiinaay dacarsittoh xiinaa kee garab dacarsittoh xiina murti kee murtisiyyo akah ossannah abak maaqiddi caabiinu diggosaanama, taamâ saami ginaanam kee bica le keefo akah ginnimtannah abaanama, tohulluk naharal qimmisimte raymitteh daddoosih taamoomi xakabaanam faxximteemih sabbata

warrayte sanootah abniseenih sugen raymi daddoosih taamoomi fayya le sahdayti ariiqo kee lakqo keenik awquk akah kibbimannah abeenim takkay immay sarrimaane keenik diggoosoonuh raymat xoqoysima ikoytiini cusol tabisak, ginô gadditte elle xiinisan tabsiyyi xoqoysim dacrisiyyaa kee esserimiyyi gexsit aracat haanam faxximteemih sabbatah,

gandaadô raymi xoqoysima daddoosen/yeyderren gadda xiinisoonuh edde yantifiqeenim kee dacrisoonuh maddur kee ayyuntiinô mantafaqiino

diggoysanam edde xiqaanah yanin amolladi ligdo dadlisaanam faxximteemih s

**አዋጅ ቁጥር 1223/2020ዓ.ም**

## የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ

የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የብዝሀ ሕይወት ሀብትን በመጠበቅ የውኃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋችን ልቀት በመቀነስ የመሬት የማምረት አቅም ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንዲተላለፍ እና በዚህም ለሰብልና ለእንስሳት ሃብት ልማት ሥራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር በማስፈለጉ፣

የአርሶ አደሩ፣ አርብቶ አደሩ እና ከፊል አርብቶ አደሩ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በማድረግ ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ መደላድል ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ቀደም ሲል የተጀመሩትን የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ማስቀጠል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤ ባለፉት ዓመታት የተከናወኑት የተፋሰስ ልማት ሥራዎች

ከፍተኛ የሰው ጉልበትና የገንዘብ ወጪ ተደርጐባቸው እንዲለሙ የተደረገ ቢሆንም ዘላቂነታቸውን ለማረጋገጥ የተፋሰሱ ተጠቃሚዎች በባለቤትነት ስሜት ተረክበው የተፈጥሮ ሀብቶችን የሚያስተዳድሩበት የርክክብ

የአጠቃቀም፣ የአጠባበቅና የተጠያቂነት አሠራር ማስፈን ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ያለሙትን ሀብት ለማስተዳደር፣ ለመጠቀምና ለመጠበቅ

ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ተጠቃሚነታቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉበትን ሁለንተናዊ አቅም ማስደግ በማስፈለጉ በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55/1/ እና /ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**Inikhaytoh Exxa**

**Amolladi Madqammudo**

**1, Ux Amottabu**

ta kukti gandaadô raymittê daddas xiinissoo kee xoqoysim kuktak ixxima 1223/2020 axcuk galab akak xagaanam duudumtah

**2, maqnisso**

Qangarak makko kali maqna teceeh akke aytek ta kuktih addal;

**1** Gandaadô rayma luula daddoosih taamah egla '' iyyaanam sinam gandaadoh rayma daddoosoonuhuuy, dacrisaanam kee edde antifiquk sinni fayxiik ittallih ginak ikoytiinul miraacisak , luulâ taamah hadaf rakiibo abak miractimaanam kee dimokraasiyyoh gital miractimah yan is xaqa madqa daga raaqiyya leh tan egla kinni

**2** Gandaadô rayma akak yaanam inki baaxoh fidoh mohoodissok caxittah tan baaxok ironnef kee addanneefik leelwa marissah tan dariifa edde tasgalleh tan qunxa qunxa raymitte kinnuuk fantiita baar akak 500 hiktarak anbe sinni baaxoh exxa kinni

**3** Gandaadô raymih daddos iyyaanam gandaado raymitteh dariifah addat geytimta xarriita,lee kee caxah samadih gadda dacrisaanam kee murtiino akak dadlisoonuh cato takkeh tan taamoomi asgallukuy sanayisa abnisaanama yaanama

4 Gandaadô raymih Xoqoysima iyyaanama eglah xissiimoonay hinnay xissiimekal raymi daddoosiyyih sababah ginniimah yan gaddi saanih takku goloq gital edde Tantifiqe ummattah exxaaxi,

**5** Agleh ikoyta iyyaanam xoqosimah sittin geyil xiinisan raymih addat cankah,doolatiinu kee doolatiinu alle sinni eglaali kee dabsimaamih gubat antiribbixxe wayte ikoytaatii kee dariifal mannowta maritte agleh lon ikoytiinut baxaabaxsale ginogaddih taamoomi taamitak daddoosak akah yantifiqen innah doolat keenih tece barri baaxo,

**6.** cankah ikoyta iyyaanam buqreh xiinaay garab dacasittoh xiina kee dacarsittoh xiina hinnammay kali madqâ gar akah yontocowwe marih gabat timtiribbixxe baaxo

**7''** doolat ikoyta''iyyaanam federal hinnammay rakaakay doolatih gubat deesimak timtiribbixeh anuk deesen baaxo qaddoosam kinnuk garbô baaxoy, dubaalaay daccarsimta baaxooxaay, doolat

**ክፍል አንድ**

**ጠቅላላ ድንጋጌዎች**

**1. አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ 1223/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል። ቁጥር

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡

1/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ሕብረት ሥራ ማኅበር" ማለት ሰዎች የማህበረሰብ ተፋሰስን ለማልማት ፣ ለመጠበቅና ለመጠቀም በፈቃደኝነት የሚያቋቋሙት በጋራ ባለቤትነት የሚያስተዳድሩት፣ በህብረት ሥራ መርህ መሠረት የሚመሩትና ዲሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚመራ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ማህበር ነው፤

2/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ማለት ወደ አንድ መልክዓ-ምድራዊ አቅጣጫ የሚፈስሱ የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ውኃዎች የሚያካልሉትን አካባቢ የሚያካትት አነስተኛ ተፋሰስ ሆኖ አማካይ ስፋቱ ከ 500 ሄክታር የማይበልጥ የመሬት ክፍል ነው፡

3/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት' ማለት በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የአፈር፣ የውሃ እና የዕጽዋት ሀብት ለመጠበቅና ምርታማነቱን ለማሳደግ የሚረዱ ተግባራትን አቀናጅቶና አጣጥሞ ማከናወን ማለት ነው፤

4/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማለት በማህበር ተደራጅተውም ይሁን ሳይደራጁ ተፋሰሱ በመልማቱ ምክንያት የሚፈጠረውን ሀብት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚጠቀሙ የህብረተሰብ ክፍሎች ማለት ነው፤

5/ የወል ይዞታ ማለት በተጠቃሚዎች ስምምነት በሚተዳደር ተፋሰስ ውስጥ በግል፣ በመንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶችና ተቋማት ያልተያዙ ይዞታዎች እና የአካባቢው ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የተለያዩ የተፈጥሮ ሀብት ሥራዎች በመሥራት አልምተው እንዲጠቀሙበት በመንግሥት የተሰጣቸው የገጠር መሬት ነው፤

6/ የግል ይዞታ" ማለት በአርሶ አደሮች ከፊል አርብቶ አደሮች እና አርብቶ አደሮች ወይም በሌሎች በሕግ መብት በተሰጣቸው ሰዎች የተያዘ መሬት ነው፣

7/ የመንግስት ይዞታ" ማለት በፌደራል ወይም በክልል መንግስት ተከልሎ የተያዘና ወደፊት የሚከለለውን መሬት የሚገልፅ ሲሆን የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት ጥብቅ ቦታዎችን የመንግስት

buqreeraay maqaadin ardetteey  kalitteetay weeqaytitte kee too gital tintiribbixeh tanim amolladissa

**8**’’baxsa le hangi faxxah tan ayyunti exxaaxi’’iyyaanam ayyuntiinoy qaafitaay maddur caalootah sababah sinni gar esseroonu geyoonuh taqabi edde garayah yan maritte, saymaraay xagar erkenna le maray alaaqa kee ermaani tonna tonna celah tan ayyunti exxaaxi kinni

9,, gabat agle iyyaanam faatacisiyyal xagoonu duudan gaddittel gar leh tan maritte faatacisiyyi macooh gexsitih addat yangaloonuh gar Aalliyya yaanama

10  ,,baxsa le asta ,,iyyaanam inki qunxa gandaadoh rayma gersi tumak baxisak yaaxigoonuuy raakaakay,rasuu kee daqar xiinissoh caydittey tonnah inayta rayma luk mannal fantaaxaw lem yascassoonuh baaxoh fidoh oytih siirata[ JIS] kee arooca elle geytimta mudooda asgagalluk yace asta kinni

11,, luulâ taamah eglah kukta ,,iyyaanam luulâ taamah kuktih ixxima 985/2009  kinni

12,, Raakaakay,, iyyaanam itiyoopiyak federaliyyoh demokrasiyyoh ripoblikik doolat madqa masayyak 37[1]akkinnaanih rakaaakay wagsissam takkay immay addisaaba kee dirdawâ maagaalah xiinissoosa ossissa

13 Menester/minister iyyaanam buqre menester/minister iyyaanama

14 Numu iyyaanam ginok nammalakli kinni hinnay kaadu madqa xagariino akah tomcowwe xagara yaanama

15 Ta kuktih addal lab nadoh tomcowwe madqa mudo say nadoh edde ayfaf tacee

**3  abbinooysiyyi maadu**

ta kuktih baaxoh addal geytimta gandaado raymittel abinal asele

እርሻዎችን፣ የማዕድን መሬቶችን ሃይቆችን፣ ወንዞችንና በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል፣

8/ ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች'' ማለት በማህበራዊ፤ በጤና ወይም በኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ምክንያት መብታቸውን ለመጠየቅና ለማግኘት ችግር የሚገጥማቸው እንደ ሴቶች አካል ጉዳተኞች፣ ሕጻናት እና አረጋውያን የመሳሰሉት የኅብረተሰብ ክፍሎች ናቸው፤

9/  ተሳትፎ ማለት በውሳኔ ሊነኩ በሚችሉ ሀብቶች ላይ መብት ያላቸው ሰዎች በውሳኔ ሰጪነት ሂደት ውስጥ የመሳተፍ መብት ማለት ነው፣

10/ ልዩ መለያ ማለት አንድን አነስተኛ የማህበረሰብ ተፋሰስ ከሌላው ለይቶ ለማወቅና ከክልል፣ ከዞንና ከወረዳ የአስተዳደር ወሰኖች እንዲሁም ከዋና ተፋሰስ ጋር እንዴት እንደሚተሳሰር ለማመላከት የመልክዓ-ምድር መረጃ ሥርዓት ጂ.አይ.ኤስ) እና የቦታዎች መገኛ ውቅሮችን (የጂኦግራፊያዊ ኮርዲኔቶችን በማቀነባበር የሚሰጥ መለያ ነው፣

11/ “የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ'' ማለት የህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ቁጥር 985/2016 ነው፤

12/ “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47(1)  የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣

13/ ሚኒስቴር ሚኒስትር ማለት የግብርና ሚኒስቴር ሚኒስትር ማለት ነው፤

14/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው፡

15 / በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው ለሴት ፆታም ያገለግላል።

**3. የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በሀገሪቱ ውስጥ በሚገኙ የማኅበረሰብ ተፋሰሶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**4 kukti hadafitte**

ta kukti ciggilta hadafitte allele

1 daariifa qassinoowiyya kee gino gaddih sellimiyya kalalak ,mango rooci kee gadda dacrisak leê gadda maqarroosak laqna taxmuume

gaazitte tufiyya aynukusuk gandaado qabaarat duffuumiyya yaynukuseenim kee yangigireenimih ligdo gablusaanama

2 sarrimaane le gandaadô raymih daddos,dacayroo kee xoqoysimiyya diggoysak baaxok amrutiyyi ligdo dadlisaanama. buqreh xiina/dacarsittoh xiinâ murtii kee murtiino akah ossannah abaanama; tonnah dayim caabiinu diggoysaanam kee taamâ saamih giniyyah bica le caalat ginaanama

3 Gandaadô raymat xoqoysimaami ikoytiini cusol gino gadditte daddoosoonuhuuy,dacrissonuh ,xiinisoonuu kee edde xoqosimoonu ken xiqsissa abini siirat aracat gacah tah gandaadô raymih xoqoysimaamik tengele ligdo dadlisaanama

**Nammeyhaytoh exxa**
**Raymi ikraaroo kee daddos**
**5, Raymi weeloola**

1. Ta kukta raakiibo abak mamaxxaga akah tomcowwe raymitteeta gandaadô raymaa kee daqar caddol baxsale inayta rayma kinni

2. akkinnaanih gandooda hinnammay inayta raymih baar kalah baaxoh fidiinaan maadu inki tamixxige daraafal geytimta gino gadda ittalluk daddoosoonu kee dudda le gital hanaawisoonuh bica le gurral hinnammay qeedalsima gital deeseenim takkem faxximta

**6.Gandaadô rayma**

1.gadaadô raymak fanti baara 500 hiktaar kinnuk deraafi elle aninnaan baaxoh daffeyna hinnimmay raymi daddoosih madma akkalat culusak giddakkiini fayyak ramma lem duudah

2.Ta masayyak lani masayyak [1] madqammudo tanay immay gandaadô raymi 500 hiktarak daga yakke waqdi toh bici elle aninnaan gurral keefaanam kee daddoosanamaay kee  hanaawisaanam xiiqimtah

**4. የአዋጁ ዓላማዎች**

ይህ አዋጅ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፤

1/ የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን በመከላከል፣ የብዝሃሕይወት ሀብትን በመጠበቅ የውሃ ሀብትን በማጎልበትና የሙቀት አማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የማህበረሰቡን ለድርቅ ተጋላጭነት መቀነስና የመቋቋም አቅምን ማሳደግ፣

2/ ዘላቂነት ያለው የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀምን በማረጋገጥ የመሬትን የማምረት አቅም ማሳደግ የአርሶ/አርብቶ አደሩን ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግ፡ እንዲሁም ለምግብ ዋስትና መረጋገጥና ለሥራ ዕድል ፈጠራ ምቹ ሁኔታ መፍጠር፡
3/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች በባለቤትነት ስሜት የተፈጥሮ ሀብቶችን ለማልማት ለመጠበቅ፣ ለማስተዳደርና ለመጠቀም የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት ማስፈን ለዚህም የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎችን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ።

**ክፍል ሁለት**
**ስለ ተፋሰስ ዕቅድና ልማት**

**5. የተፋሰስ ዓይነቶች**

1/ በዚህ አዋጅ መሠረት እውቅና የተሰጣቸው ተፋሰሶች የማህበረሰብ ተፋሰስና በወረዳ ደረጃ የሚለይ ዋና ተፋሰስ ናቸው።

2/ የማንኛውም የማህበረሰብ ወይም ዋና ተፋሰስ ስፋት ወይም መልክዓ-ምድራዊ ወሰን በአንድ ውስን አካባቢ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብት በአንድነት ለማልማትና ብቃት ባለው መንገድ ለመንከባከብ አመች ወይም ተመጣጣኝ ሆኖ የተከለለ መሆን አለበት።

**6. የማህበረሰብ ተፋሰስ**

1/ የማህበረሰብ ተፋሰስ አማካይ ስፋት 500 ሄክታር ሆኖ እንደ አካባቢው መልክዓ- ምድራዊ አቀማመጥ ወይም የተፋሰስ ልማቱን ዓላማ ግምት ውስጥ በማስገባት መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም የማህበረሰብ ተፋሰሱ ከ 500 ሄክታር በላይ : በሚሆንበት ጊዜ ይህንኑ እንደ አመችነቱ ከፋፍሎ ማልማትና መንከባከብ ይቻላል።

3. Ta  masayyak lani masayyak [2] madqammudo.tanay immay kuraakuriyyi sabbatal ginniimah yan raymi baar 200 hiktaarak adda yakkem maduuda

**7 <u>inayta rayma</u>**

1. Inaytâ rayma akak iyyaanam inaytâ raymitteh kobox kinnuk baar akak 20000 hektaar gufu duuda

2. Ta masayyak lani maasayyak[1] madqammudol galab akak xageenim  tanay immay dariifâ daffeyna elle taninnal anuk hinnay xiinissô bicih taagah giddakkiini fayyak ramma lem bictah

3 inaytâ raymitteeta daqar addal geytimta giffagiffo le weeqaytittek ugutak baxisaanah

4.Inaytâ raymak baxsimmayeenih tewqeh tan gandaado raymitteeta daddoosoonuh raymak dagah exxak qimmisak guba raqta exxa fan yaakumik ciggiilil oobaanam faxximta

5.Ta masayyak lani maasayyak [4] madqammudo elle taninnal anuk amogginak addah xaban kee xabanal geytimta gandaado raymitteeta nahal daddoosanam qassinoowiyyi caddol sahdayti cayla kee gaddi xayyos akkalat culusak daddoosaanam faxximta raymitteeta baxsaanamih nahasiino amcawwele

**8  <u>gandaadô raymih ikraaroh bica</u>**

1.gandaadô raymih ikraaroh bici gabat agliino kee madqa kattaatam faxximta

2. wagatah yan xagar faataciseh yan baaxo xoqoysimiyyih siiratal elle abbinoowu waa dariifal baaxo xoqoysimih ikraaro takkeh gandaadô raymih ikraaro tohuk ugut abaanam keenil tan

3 gandaadô rayma daddoosa xagar naharak gandaadô raymih ikraaro bicisaanam keenil tan

4.Gandaadô raymih daddoosuk ugut takke ikraaro bictam  luula taamah egla soolisanamak naharal kinnuuk luulâ taamah egla bicissah tan makaado raymi xaqoysimaamih missoyna bicisoonuh xaban kee xabanah wagitah yan buqrê maktabat cattiimak ikraaro bicisaanam keenil tan

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተደነገገው ቢኖርም በመከፋፈሉ ምክንያት የሚፈጠረው ተፋሰስ ስፋት ከ200 ሄክታር በታች ሊሆን አይችልም።

**7. <u>ዋና ተፋሰስ</u>**

1. ዋና ተፋሰስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስብስብ ሲሆን ስፋቱ እስከ 2000 ሺ ሄክታር ሊደርስ ይችላል።

2.በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው ቢኖርም እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ ወይም ለአስተዳደር አመችነት ሲባል መጠኑ ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ይችላል።
3/ ዋና ተፋሰሶች በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና ወንዞችን መነሻ በማድረግ ይለያሉ።

4/ ከዋና ተፋሰሱ ተለይተው የወጡትን የማህበረሰብ ተፋሰሶች ለማልማት ከላይኛው የተፋሰሱ ክፍል በመጀመር ወደታችኛው በቅደም ተከተል መውረድ ያስፈልጋል።

5/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (ጠ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከራስጌ በታች ጎንና ጎን ከሚገኙ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በቅድሚያ የሚለማውን የመራቆት ደረጃ፣ የሰው ሀይልና የሀብት አቅርቦት ግምት ውስጥ በማስገባት ሊለሙ የሚገባቸው ተፋሰሶችን የመለየት ቅድሚያ ይሰጣል::

**8. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት</u>**

1/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ ዝግጅት የአሳታፊነት መርሕን የተከተለ መሆን አለበት።

2/ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የመሬት አጠቃቀም ሥርዓት ተግባራዊ በሚሆንባቸው አካባቢዎች የመሬት አጠቃቀም እቅዶች በሚኖሩበት ጊዜ የማህበረሰብ ተፋሰስ እቅዶች እነዚህኑ መነሻ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡
3/ የማህበረሰብ ተፋሰስ የሚያለሙ አካላት በቅድሚያ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ "ማዘጋጀት አለባቸው፡፡

4/በ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት መነሻ ዕቅድ የሚዘጋጀው የህብረት ሥራ ማኅበር ከመቋቋሙ በፊት ሲሆን የህብረት ሥራ ማነበሩ መሥራች ኮሚቴ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበሩን ከማደራጀት ጎን ለጎን በሚመለከተው የግብርና ጽ/ቤት በመታገዝ ዕቅዱን ማዘጋጀት አለበት።

5 Bictah tan ikaaro addat yasgalleenih yanin abinitte daariifah qassinow kee ginô gaddih selliimiyya kalaloonuhuuy,lee gadda gablusoonu kee laqna taxmuume gaazitteh tufiyya aynukusuk,baaxoh amrutiyyih ligdo dadlisoonu xiqsissam takkem faxximta

5/ በሚዘጋጀው ዕቅድ ውስጥ የሚካተቱ ተግባራት የአካባቢ መራቆትንና የተፈጥሮ ሀብት መመናመንን ለመከላከል፣ የውኃ ሀብትን ለማጎልበትና የሙቀት ኣማቂ ጋዞችን ልቀት በመቀነስ የመሬትን የማምረት አቅም _ ለማሳደግ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው።

6.Gandaadô raymih daddos ikraarimah yan waqla inkih Tanih tan raymitte daddoosoonuh xiqsiisah yan bica abak garab daddoosimmay geeri garab daddoosimekal raaqaamak faxximta dacayri abaanam faxximta.

6/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት በሚታቀድበት ጊዜ መላ ተፋሰሱን ለማልማት የሚያስችል ዝግጅት በማድረግ ከፊሉ ለምቶ ከፊሉ ሣይለማ እንዳይቀር ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

7.inaytâ raymi gandaado raymitteh kobox kinnuk daddos ikraaroh abbinoowiyyi qax yamqeggidah elle faxxiiminnaanih innal gandaado raymih baarih giddakkiinu baxaabaxissa heenih bicisaanam keenil tan

7/ ዋና ተፋሰስ የማህበረሰብ ተፋሰሶች ስብስብ በመሆኑ ለልማት ዕቅዱ ተፈፃሚነት ያመቾ ዘንድ እንደ አስፈላጊነቱ በማህበረሰብ ተፋሰስ ስፋት መጠን ተከፋፍሎ መዘጋጀት ይኖርበታል።

8 Ginook rayma xintoh caydih baxsa yabluuseh yan gandaado raymal bicisaanah yanin ikraaro gadaadô caydu rakiibo abak inkih tan raymi xoysima gandaadoh gabat aglel tekkem takkam faxximta .

8/ በተፈጥሮ የተፋሰስና የአስተዳደር ወሰን ልዩነት በሚያሳይ የማህበረሰብ ተፋሰስ ላይ የሚዘጋጀው ዕቅድ የተፋሰስ ወሰንን ተከትሎ ሲሆን ሁሉንም የተፋሰስ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ያሳተፈ መሆን አለበት።

9 gandaado raymih daddoosih ikraaroh bicsiyyi dariifah ayyuntiino sarrimaanê gexsit kattateh yanim faxximta

9/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ዕቅድ አዘገጃጀት የአካባቢና ማኀበራዊ ዘላቂነት መርሕን የተከተለ መሆን አለበት።

10. inki gandaado raymi xalantot qokkolsimma iyyeh;kibbiimeh anuk 5-10 sanat fanah xer widdiirih ikraaro yaallem faxximta

10/እንድ የማህበረሰብ ተፋሰስ በካርታ የተደገፈ የተሟላ ከ፭ እስከ ፲ ዓመት የረዥም ጊዜ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል።

11. Ta maasayyak lani maasayyak[9] madqamudumtem elle taninnal anuk gandaado raymitteeta xer waktih tan ikraaro rakiibo abeh anuk liggidi ikraaro keenih bicisaanam faxximta

11/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የማህበረሰብ ተፋሰሶች የረጅም ጊዜ ዕቅዳቸውን መሠረት ያደረገ ዓመታዊ ዕቅድ ሊዘጋጅላቸው ይገባል።

12.Gandaadô raymih ikraaro baaxok inayta raymih istirateejih ikraaro bicisoonuh madqal abbootan akah Yomcowweh yan xagar yeyyeeqeh yan ikraaro rakiibo abam kaal tan

12) የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ አገራዊ ዋና የተፋሰስ ስትራቴጂክ ዕቅድ ለማዘጋጀት በህግ ሥልጣን በተሰጠው አካል የወጣ ዕቅድን መሠረት ማድረግ ይኖርበታል

13. Gandaadô raymih daddosih luulâ taamah egla bicisseh tan ikraaro inki daqaarak iroh maaduk taturam tekkek ikraaro caagid wagsiisah yan daqoorul inkih xayyowwa iyyeh daqor buqreh makaatibih sittin geyil faatacsimam faxximta

13/ በማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ማኀበሩ የተዘጋጀው ዕቅድ ከአንድ ወረዳ በላይ ወሰን ተሻጋሪ ከሆነ ዕቅዱ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ወረዳዎች ሁሉ ቀርቦ በወረዳዎቹ ግብርና ጽ/ቤቶች ስምምነት መጽደቅ አለበት።

14.kulli dariifal baxsu leh tan gandaado raymitteeta kee inayta raymitteeta baaxoh caddol baxsu le baxsih macoh gexsit kattaatak baxsu le baxsa keenih yaceenim faxximta

**9 . <u>Gandaadô raymih daddoosu</u>**

1 Gandaado raymih daddoosih taamoomi daga raaqa raymak qimmisak guba raaqa raymih exxa fanah oobam faxximta

2. Gaddoosima raymah bictah tan teknolojitte doorak elle faxximtannal absiisaanam faxximta

3.Gandaado raymitteeta raymit xoqoysimaay,doolataay, hinnammay kaadu doolat xagar aalle sinni missoynaani ginnimtah tan porojektittet ,hinnay kaadu cankooki gabat daddoosimtu duddah

4.Gandaado raymih ikraaro gino rayma kee xiinissô maadih fanat baxsi elle yanih yan aracal rada waqla ikraaro abinal assu duddam xiinisso maadu kattaatak akkele

5. raymi daddoosih tamoomil xaariya kee dalka lowsiisoonuh rayma kee daddos tamoomal xaariya kee dalka lowsiisoonuh ogoysimte kalali cogdaadit yantifeqeenim faxximta

6.Gandaadô rayma daddoosah yan mari edde yantifiqeenih yanin gaba abtah tan sasnisa celtah tan kemikal satqo akak geyaanam doolat akkiiy madqa idni akah teceeh tan missoynaani cagalah akkele

7. faxe xaariya sad kemikal xoqoysil asah yan waqdi diidaaleh andoyaay dorbaa kee dariifal biyak baahaamak kemikal keefiyah yan madqa xagar kemikaalat xaqoysimah yan marah dudda le ixxiga yaceenih,elle faxxiima waqdi kee xaqoysimiyyi waqla doorra heenih niifiyya akah gexsiisan innah absiisaanama ,diidaaleh andora aba marah kemikal niifiyyi yakkek nahal yaakume takkaawisiyyih abinnitte yagdubeenim faxximta

14/ በየአካባቢው የሚለዩ የማህበረሰብ ተፋሰሶች እና ዋና ተፋሰሶች አገራዊውን የልዩ መለያ እሰጣጥ ሂደት ተከትለው ልዩ መሊያ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

**9. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት</u>**

1. የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ከላይኛው የተፋሰሱ ኣካል ወደታችኛው የተፋሰሱ ክፍል ሥራዎች ተጀምረው መውረድ አለባቸው።

2. ለሚለማው ተፋሰስ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ በአግባቡ መተግበር ያስፈልጋል።

3/ የማህበረሰብ ተፋሰሶች በተፋሰሱ ተጠቃሚዎች፣ በመንግሥት ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች በሚቋቋሙ ፕሮጀክቶች ወይም በግለሰቦች ሊለሙ ይችላሉ።

4/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ዕቅድ በተፈጥሮ ተፋሰስና በአስተዳደር ወሰን መካከል ልዩነት ባለው ቦታ ላይ የሚያርፍ በሆነ ጊዜ ዕቅዱ የሚተገበረው የአስተዳደር ወሰንን በመከተል ይሆናል፡፡

5/ በተፋሰስ ልማት ሥራዎች ላይ ተባይና በሽታን ለመቆጣጠር የተቀናጁ የመከላከያ ዘዴዎች ይተገበራሉ።

6/ የማህበረሰብ ተፋሰስ አልሚዎች የሚገለገሉበትን ማናቸውም ሰው ሠራሽ ማዳበሪያ ወይም መሠል ኬሚካላዊ ግብዓት የሚያገኙት ከመንግሥት ወይም ሕጋዊ ፈቃድ ከተሰጣቸው ድርጅቶች ብቻ ይሆናል

7/ ማንኛውም ፀረ-ተባይ ኬሚካል ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ ሁሉ በንብ እርባታ በሰብልና በአካባቢው ላይ ጉዳት እንዳያስከትል ኬሚካሉን የሚያሰራጨው ሕጋዊ አካል ለኬሚካሉ ተጠቃሚዎች በቂ ዕውቀት ማስጨበጥና ተገቢውን ወቅትና የአጠቃቀም ጊዜ መርጠው ርጭቱን እንዲያካሂዱ ማድረግ ይኖርበታል። ለንብ አርቢዎችም ርጭቱ ከመደረጉ በፊት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ተግባራት መፈፀም አለባቸው::

8.ta masayyak lani masayyak gubal tan madqam mudo elle taninnal anuk inki inki kemikaalitte leh tan gibdi summittek ugutak caxah samad kee dariifal baahah yan taqabi giffo leemih sabbatah mihrat li qokolut cattiimak akah niifan innah hinnammay kaak xayi kattaatiyyih catol xoqoysil akah asannah absiisaanama tonnah wasaakat xagarat le tumammi elle kalan gurra dariifa dacayrih madqa dacrisak faxximah yan takkaawisiyya abaanam keenil tan

9.Gandaado raymih dariiifah addal xoqosil assah ta satqo.mexxat akak daccarsimeeh xaqoysiyyi widdir akak tatre wee yakkem faxximta

10.Gandaado rayma daddoosah yan mari gino buqreh satqo akah xoqoysiman innah ken elsiisaanama

## Sidichaytoh exxa

## Gandaaado raymat xaqoysimah luula taamah egla elle gina

### 10 . Luula taamah eglah giniyya

1.Luulâ taamah eglah madqammudo elle taninnal anuk sidichaytoh exxal muden madqammudo abinal asele

2. rakiiboh egla gandaadô raymih baar hinnammay maadu rakiibo abak ginniimam faxximta takkay ikkal gandaado rayma kee xiinisso maaditte sissinaane tellek egla daqar maadu kattaatak ginnimam faxximta addafakoot edde xintal madqimele

3.Gandaaado raymih daddos luula taamah tiyantitte rasi xintoh maadu kattaatak ginniimeloonum akkuk rasi addat sitta celta abinitte tiyaak daga gandaado raymih daddos luula taamah tiyanti yanim maduuda

4.Gandaadô raymih daddoosih luula taamah federeshinitte rakaakay maadu kattaatak ginniime loonum kinnuk rakaakay addat sitta celta taamal tiyaak daga yakkoonu maduudumta.

5. Elle faxximtannal baaxoh caddol inki gandaadô raymih daddoosih luula taama federeshin ginniimam duudah

8/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ስር የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አንዳንድ ኬሚካሎች ካላቸው ጠንካራ መርዛማነት የተነሳ በዕፅዋትና በአካባቢው ላይ የሚያደርሱት ጉዳት ከፍተኛ በመሆኑ በባለሙያ ድጋፍ እንዲረ ወይም በእርሱ የቅርብ ክትትል ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግና የቅሪቶች አወጋገድ የአካባቢ ጥበቃ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ተገቢው ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

9/ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ ግብዓቶች ደረጃቸውን የጠበቁና የመጠቀሚያ ጊዜያቸው ያላለፈ መሆን ኣለበት።

10/ የማህበረሰብ ተፋሰስ አልሚዎች ተፈጥሯዊ የግብርና ግብዓቶችን እንዲጠቀሙ ይበረታታሉ።

## ክፍል ሦስት

## ስለማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አመሠራረት

### 10. ስለ ህብረት ሥራ ማኅበር አመሠራረት

1/ የኅብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በክፍል ሦስት የተደነገጉት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ።

2/ መሠረታዊ ማኅበሩ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ስፋት ወይም ወሰን መሠረት መቋቋም አለበት። ሆኖም ግን የማህበረሰብ ተፋሰሱና የአስተዳደር ወሰኖች የሚለያዩ ከሆነ ማኅበሩ የወረዳውን ወሰን ተከትሎ መቋቋም አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

3/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ዩኒየኖች የዞን አስተዳደር ወሰንን ተከትለው የሚደራጁ ሲሆን በዞን ውስጥ በተመሳሳይ ተግባር ከአንድ በላይ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ኣይችልም። ሥራ ዩኒየን ሊኖር

4/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ፌደሬሽኖች የክልል ወሰንን ተከትለው የሚደራጁ ሲሆን በክልል ውስጥ በተመሳሳይ ተግባር ከአንድ በላይ ሊኖር አይችልም፣፣

5/ እንደአስፈላጊነቱ በአገር ደረጃ አንድ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ፌደሬሽን ሊደራጅ ይችላል።

6 / Egla keskes kee edde xinta raymi ikoytiinu luk mannal daddoosanamaay mannal xiinisanamaay mannal dacrisaanam kee edde xoqoysimoonuwaan inni addafakoot luk daffeesoonuwaan madqamudo elle taninnal anuk xaqoysimtah tan gandaado elle walaleenih sittin gey elle gufen inna takkem faxximta

7.Gandaadô raymih xaqoysima luula taamah egla faxximtah tan miizaanisiyyi xiqsiisentitte kibba heenih xayyoowak luula taamah kukta rakiibo abak celtah tan abbatiinok madqa xagariino geele

8.raymak geytimtah tan gino gaddih xalitte innawak qaysooy,garboo kee garbot geytimta xalitte hinnammay tonna tonna celta gino gaddih xalitteeta qaynatal takku lakqoh aylammuk geytimteh tan lakqok adoytiitih kuraabiyaanam kee raymi daddoosih hadafah eglâ migaaqal fakkiimu waa banki cisaaabal daffeytu wayta lakqo qadad eglah addah edde xintal madqimele

**11.raymi xoqoysimah eglah adotiiti**

Ciggiltah tan xiqsiisentittek tiyak teena kibtu wayta itiyopiyyiinu ta kukta rakiibo abak raymi xoqoysimah luula taamah eglah adoyata yakkeemih gar lon

1 Raymi rakaakayih addat baaxoh ikoytiinu leh yan maray tokkek geytima culentat mannoowa;

2 .Raymi rakaakayih addat baaxoh ikoytiinu aalle waanamah dariifal sigah yan mara kinnuk gino gaddat xoqoysima yekkeenik;

3. Elle geytimaanam raymi rakaakay akke wayta baaxo mardeysiteh yan mara takku kalah madqa gital raymâ luk angaaraw leh ta maritteta

4.luulâ taamah eglah kuktal madqamudol elle taninnal anuk gandaado raymih dariifal baaxoh ikoytiinu leeh, 18 karmak addah yanih yan mari qarsi xaleyna katuuk yaysaqarrimeenim duudaanah

5. Ta maasayyal madqam mudumtem xiqsiisentitte kibeh geytime maraa kee baxsa le hangi akah faxxiima ayyunti exxaaxi luulâ taamah adoyta yakkeeh eglat geytimah yan tuxxiiqittet agleyta yakkuh dudda le gar lon

6/ የማኅበሩ መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ ተፋሰሱን በባለቤትነት ይዘው እንዴት እንደሚያለሙት ፡ እንደሚያስተዳድሩት እንደሚጠብቁትና እንደሚጠቀሙበት በዝርዝር የሚደነግግ ሆኖ ተጠቃሚ ማህበረሰቡ የመከረበትና ስምምነት ላይ የደረሰበት መሆን አለበት።

7/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኀበር አስፈላጊ መመ በኛ መስፈርቶችን አሟልቶ በመቅረብ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ መሠረት አግባብ ካለው ባለሥልጣን ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል።

8/ ከተፋሰሱ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች እንደ ሣር ደን እና የደን ውጤቶች ወይም መሰል የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች በዓይነትም ሆነ በገንዘብ ተሸጠው ከተገኘው ገንዘብ ላይ ለአባላት የሚከፋፈልና ለተፋሰሱ ልማት ዓላማ በማኀበሩ ስም በሚከፈት የባንክ ሂሳብ ተቀማጭ የሚሆነው የገንዘብ መጠን በማኀበሩ የውስጥ ደንብ ይወሰናል።

**11. <u>ስለተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማህበር አባላት</u>**

ከሚከተሉት መስፈርቶች አንዱን የሚያሟሉ ኢትዮጵያውያን በዚህ አዋጅ መሠረት የተፋሰስ ተጠቃሚዎችህብረት ሥራ ማህበር አባል ለመሆን መብት አላቸው፡

1/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የመሬት ይዞታ ያላቸውና ከዚሁ በሚገኝ ገቢ የሚተዳደሩ

2/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የመሬት ይዞታ ባይኖራቸውም በዙሪያው ነዋሪዎች ከመሆናቸው የተነሣ ኩተፈጥሮ ሀብቱ ተጠቃሚዎች የሆኑ ወገኖች፣

3/ ኗሪነታቸው በተፋሰሱ ክልል ውስጥ ባይሆንም መሬት ተከራይተውም ሆነ በሌላ ህጋዊ መንገድ ከተፋሰሱ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰዎች።

4/ በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው ቢኖርም በማህበረሰብ ተፋሰስ በተፋሰስ ክልሉ ውስጥ የመሬት ይዞታ ያላቸውና ዕድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች የሆኑ ሰዎች በሞግዚቶቻቸው አማካኝነት በአባልነት ሊመዘገቡ ይችላሉ።

5/ በዚህ አንቀጽ የተደነገጉትን መስፈርቶች አሟልተው የተገኙ ልዩ ትኩረት የሚያሻቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የህብረት ሥራ ማህበሩ አባል የመሆንና ማኀበሩ የሚያስገኛቸውን ጥቅሞች ተካፋይ የመሆን ሙሉ መብት አላቸው።

**12.Gandaadô raymat xoqoysimah eglat kunnabna le adoytiiti**

1.Raymi xoqoysimah egla madmah abbinoowiyyah cato abtaah raymi dariifal saanih tan xoqoysima akke sinni cankookiiy,eglaaliiy kalah dabsimaami massakkaxxa le adoytiinuh oggolaanam duudaanah.
2. massakaxxa le adoytit raymat xoqoysimah eglah addat doorimaanam takku dooraanam hinnammaya akinnaanih caagidil anay yaceenimih gar yaalloonu maduudan

**13 Massakaxxa le adoytiitih doori kee qaaqa**

1.massakaxxa le adoytit isinni fayxiik ugutak hinnammay gandaado taama selta makaadoh esserok ugutak gino gaddih daddos dacayri wagsiisak baritto kee fayu aceeloon, tonnah tekniikiiy qaynat kee lakqô qokol abelon

2.massakaxxa le adoytit raymi taama gexsissah tan makaadok keenil xayyowta seeco rakiibo abak amolladi koboxut akah yangalen innah abak isinni mabla aceelon

**14. Gandaadô raymih xoqoysimak luula taamah eglah adoytiitih gara**

Luula taamah eglah kukti madqamudumtem elle taninnal anuk raymi xaqoysima luula eglah adoyti kataytah tan garwa aalle le

1.ta kuktih maasayyak 23 kee 24 tan madqamudooda elle taninnal anuk gandaadô raymih addat geytimtah tan gino gadditte ittallih hinnammaya caglah edde xoqoysimaanama

2. egla gubat adoytit lon duddittek ugutak loonuh yanin mahrat takku fayxiik ugutak xoqoysimâ butta ginak rayma biyaake waa gurral culenta geysissah tan taamoomil taamitaanama

3.Ta maasayyak lani maasayyak [2] rakiibo abak culenta geysissa taamoomi,diidaaleh aydorraa, can kee canti xalu massoosaanam kee xayyoosaanamaay ,saq gablusaanam boco akke sinni garbo xalitte yamruteenim kee xayyoosaanam,caxaaxuwa kee caxa fexxitte yamruteenim kee xayyoosaanamaay, tonnah qalaftah innah yan daddos wagsissa raymi daddos biyaake wayta tamoomi amommissa.

**12. ስለማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበር የክብር አባላት**

1/ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ማኅበር | ለዓላማው ተፈፃሚነት የሚያግዙ ሆነው በተፋሰሱ አካባቢ የሚንቀሳቀሱ ነገር ግን የተፋሰሱ ቀጥተኛ ተጠቃሚ ያልሆኑትን ግለሰቦች ድርጅቶች ወይም ተቋማት በክብር አባልነት ሊቀበል ይችላል፡፡

2/ የክብር አባላት በተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ማኅበር ውስጥ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ ወይም በማናቸውም ጉዳይ ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

**13. የክብር አባላት ሚና እና ኃላፊነት**

1/ የክብር አባላቱ በራሳቸው ተነሳሽነት ወይም በማኅበሩ ሥራ አስፈጻሚ ጥያቄ ስለተፈጥሮ ሀብቱ ልማትና ጥበቃ ትምህርትና ምክር ይለግሳሉ፤ እንደዚሁም የቴክኒክ የዓይነትና የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋሉ::

2/ የክብር አባላቱ በተፋሰሱ ሥራ አመራር ኮሚቴ በሚቀርብላቸው ጥሪ መሠረት በጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባዎች እንዲሳተፉ በማድረግ ሀሳብ ይሰጣሉ፡፡

**14. <u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ</u>**

**<u>ማኅበር አባላት መብት</u>**

በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡

1/ የዚህ አዋጅ አንቀፅ 23 እና 24 ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በማህበረሰብ ተፋሰስ ውስጥ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች በጋራ ወይም በግል የመጠቀም፣

2/ በማሀበሩ ሥር አባላት እንደሙያቸውም ሆነ ፍላጎታቸው የተጠቃሚዎች ቡድን በመፍጠር ተፋሰሱን በማይጎዳ ሁኔታ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ የመሰማራት፤

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት ግቢ የሚያስገኙ ሥራዎች እንደ ንብ ማነብ፣ ወተትና የወተት ተዋፅኦ ማቀነባበር እና ማቅረብ፣ እንስሳት ማድለብ፣ እንት ነክ ያልሆኑ የደን ውጤቶች ማምረት እና ማቅረብ፣ አትክልት እና ፍራፍሬ ማምረትና ማቅረብ እንዲሁም አንደ መኖ ልማት ያሉ የተፋሰስ ልማቱን የማይጎዱ ሥራዎችን ያጠቃልላል፤

4.Gandaadô raymih daddos dacayri kee xoqoysimiyyal ambad exxiga elle geyan gugudut yangaleenimi

**15 <u>Eglah adoytit akke sinniih, gandaadô raymat xoqoysima marih garwa</u>**

1.Gadaadô raymih addat cankah hinnammay gandaadoh hinnay madqâ xagar diggoyseh yan agleh ikoytah bagul yanih yan gino gaddittet yantifiqeenimi

2. Adoyta yakkoonuh xiqsiisentitte kibeenik akinnanih waqla gandaadô raymih xoqoysimak luula taamah eglah adoyta yakkeemih gar le.

3.Gandaadô raymih daddosih dacayrii kee xaqoysim wagsissa cubbi kee ixxiga elle geyaanah yanin gudgudittet yangaleenimi

4.Egla, raymi daddoosu luK yan angaarawat axawah tan agdaabeh abinih sababal cankah ikoytal tamaatu dudda gibdaabinitte dacrisaanama

**16. <u>Gandaadô raymih xoqoysimaaami luula taamah eglah adoytiitih dirki</u>**

Gandaadô raymih xoqoysimah luula taamah adoyta yekke num luula taamah eglah kuktal madqammudunte dirkiika keenik elle taninnan innal anuk katayta dirkiika keenil tan

1.Raymi addat gexsitah yanih yan gino gaddih daddoosut gabah assagolla yaallenimi

2.Raymi dariifal tanih tan ginoo kee daddoosut geytimte gadditte finqak cataanah kalalaanama

3.Eglah edde xintaak ugutak madaqaanah yanin adoytiini ofya meklaanama

4. Egah edde xintaak ugutak cankah,buttah inkih tan abaanah yanin taamoomil abaanah yanin walalay ikraaro bicaay dacayro ddaddos abinittel abaanah yanin mano caagiida elle biyaake waa gurral ariiqô taama abaanam edde anuk cubbi luk edde yangaleenimi

5.Qedeb akak faxxiima sissin gino gaddih daddos rakiibo abak daddoswa qedeb heenih sarrimaane le manfaqat yaceenim bisoh akah inta inna egla tayyaaqeh tan ikraaro rakiibo abak qedeb taama dacaraanama

4/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት፣ጥበቃና አጠቃቀም ላይ የግንዛቤ ዕውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች የመሳተፍ፡፡

**15. <u>የማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰሱ</u>**

**<u>ተጠቃሚዎች መብቶች</u>**

1/ በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በግል ወይም በማህበረሰቡ ወይም በህጋዊ አካል በተረጋገጠ የወል ይዞታ ላይ የሚገኙትን የተፈጥሮ ሀብቶች የመጠቀም፤

2/ አባል ለመሆን የሚያሰፈልጉ መስፈርቶችን ካሟሉ በማንኛውም ጊዜ የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበር አባል የመሆን፣

3/ የማህበረሰብ ተፋሰስን ልማት፣ ጥበቃና አጠቃቀም በሚመለከት ግንዛቤና ዕውቀት በሚያስጨብጡ መድረኮች ላይ የመሳተፍ፤

4/ ማህበሩ ከተፋሰሱ ልማት ጋር በተያያዘ በሚያከናውኗቸው ተግባራት ምክንያት በግል ይዞታ ላይ ከሚከሰት ጉዳት የመጠበቅ፣፡

**<u>16. የማሀበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባላት ግዴታዎች</u>**

የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማኅበር አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገጉ ግዴታዎች እንደአግባብነታቸው መፈፀማቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩበታል፡-

1/ በተፋሰሱ ውስጥ በሚካሄድ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ላይ የመሳተፍ፣

2) በተፋሰሱ ክልል ያሉትን ተፈጥሯዊና በልማት የተገኙ ሀብቶች ክውድመት የመጠበቅና የመከላከል፣

3)በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚወሰን የአባልነት ክፍያ የመክፈል፣

4)በማኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በግል በቡድንና በአጠቃላይ በሚከናወኑ የውይይት፣ የዕቅድ ዝግጅት፣ የጥበቃና የልማት ተግባራት ላይ የኑሮ ሁኔታቸውን በማይጎዳ መልኩ የጉልበት አስተዋጽኦ ማድረግን ጨምሮ በንቃት የመሳተፍ

5)ጥገና የሚያስፈልጋቸውን ልዩ ልዩ የተፈጥሮ ሀብት ልማት መሠረተ ልማቶች፣ ተጠግነው የዘወትር ጥቅም መስጠታቸውን እንዲቀጥሉ ማኅበሩ በሚያወጣው ፕሮግራም መሠረት በጥገና ሥራ ላይ የመሰማራት።

6.Adoyta akke sinni canka gaddalola baaxol gidaabina katassu dudda abinittet asewaanama

6) አባል ባልሆኑ የግል ባለይዞታዎች መሬት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ተግባራት አለማከናወን።

**17 Eglah adoyta akke sinni gandaadoh raymit xoqoysimâ dirkiiki**

1 Agleh ikoytah bagul xaqoysima yakkeeniggedih daddos dacayri taamoomit eglah adotiiti luk faxximma inta gabatassagolla yaallenimi

2.Gandaadoh rayma biyaktu dudda abinitte yagdubeenimik issi waasanama

3 Cankah ikoytah bagul geytima gino gadditteh xoqoysimiyyi nagaynaan biyaakelem tekkek ginô gadda qassinoowiyya kataase akah waannah cubbi abitaanama

4.Rayma kee dariifal geytimta garbo gaddal giraa kee tonna celta qawwalayla ugutta waqla egla abtah tan daddos kee dacayrih angagoyyat koobahsimaanamih dirki keenil tan

**17. የማህበሩ አባል ያልሆኑ የማህበረሰብ ተፋሰሱ ተጠቃሚዎች ግዴታዎች**

1/ በወል ይዞታ ላይ ተጠቃሚ ለመሆን የልማትና የጥበቃ ተግባር ላይ ከማህበር አባላት እኩል ተሳትፎ የማድረግ፤

2/ የማህበረሰብ ተፋሰስን ሊጎዱ የሚችሉ ተግባራትን ከመፈፀም መቆጠብ፣

3/በግል ይዞታቸው ላይ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም የተፋሰሱን ደህንነት የሚጎዱና የተፈጥሮ ሀብት መራቆትን የሚያስከትሉ እንዳይሆኑ ጥንቃቄ ማድረግ፡

4/ በተፋሰሱና በአካባቢው በሚገኝ የደን ሀብት ላይ እሳትና መሰል አደጋ በሚከሰት ጊዜ ማህበሩ ለሚያደርገው የልማትና የጥበቃ እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ ይኖርባቸዋል።

**18 Adoytiinuuk diiriyimiyya**

Gandaadô raymih adoytah yan num luulâ taamah eglah kuktal akah madqammudemtenni elle yaninnal anuk ta kuktih maasayyak 11 baxxaqsimteh tan xiqsiisentit widdir gexsitih addat kibbiimekkah raaqeki adoytiinuk diiriyimah

**18. ከአባልነት ስለመሰናበት**

የማህበረሰብ ተፋሰስ አባል የሆነ ሰው በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ ፲፩ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በጊዜ ሂደት ሳያሟላ ቀርቶ ሲገኝ ከአባልነት ይሰናበታል።

**19 Egla xissiimiyya**

Egla, tahaak baxxaqsimte xisne allele

1/ Eglak amolladi koboxu

2/taama gexsissa makaado

3/faxxiimak maacissek kali lani makaadooda

**19. የማኅበሩ አደረጃጀት**

ማኀበሩ ከዚህ በታች የተገለፀው አደረጃጀት ይኖረዋል፣
1/ የማኅበሩ ጠቅላላ ጉባዔ፡

2/ የሥራ አመራር ኮሚቴ

3/ እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ንዑሳን ኮሚቴዎች።

**20.Egla kalah tan xagoorâ luk taalluwaa angaaraw**

1.Awdâ xiinissô luk saanih angaaraw ginok faxximah yan qokol geytam duddah

2.dariifal tangagayyeh tan exxaaxi takku gersi doolatiini xagar aalle sinni missoynaani hinnay eglaali luk eglah hadaf arac xagisoonuh cato takkeh tan sittigeyitteeta abaanam duudaanah

**20. ማኅበሩ ከሌሎች አካላት ግንኙነት ጋር ስለሚኖረው**

1.ከቀበሌ አስተዳደሩ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት በመፍጠር አስፈላጊውን ድጋፍ ማግኘት ይችላል።

2. በአካባቢው ከሚንቀሳቀሱም ሆነ ከሌሎች መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወይም ማኅበራት ጋር የማኅበሩን ዓላማ እውን ለማድረግ የሚያግዙ ስምምነቶችን ሊያደርግ ይችላል።

3.inki yekeesen taama mekelak hinnay mekla maleh yagduboonuh sissin xagoora luk ambalal abaanam xiiqaanah

**Ferey haytoh exxa**

**<u>Gandaadô raymih dacariiy xiinissô xoqoysimi</u>**

**21.<u> Raymi daddoosih taamoomah dacayriiy,xiinisso kee xoqoysimi</u>**

<u>1/</u> Barri baaxoh ikotiinih garwaa kee dirkiika wagsiisak kali madqqooqik madqamudooda elle taninnal anuk akkinaanih raymi addat geytimta cankah hinnammay agleh lon baaxo ginô weelo xarriita kee lee dacayrih taamoomi agdubuk hanaawisakay tonnah qedebak xarrita corriime kalaloonuh, xarriita meqaane dacrisaaman keenil tan

2,Akkinnaanih cankah hinnammay agleh lon ikoyta;

A.raymi addat tekkeh tan daddos taamoomil gibdaabini gufaamak faalitoh saqa dacrisaanamih qaaqa keenil tan

B.Raymi addat geytimtah tan baaxoh ikotitteh cayduuy buqree kee giti dariifaay,qalaftah coox lee meqe caxa samaditte daabisaanamaay hanaawisaanam kee dacrisak dariifah xarriiti maqaane kee qaafiyat dacrisaanamih dirki keenil tan

C. Raymi addat geytimtah tan ikoytiinut axawah tan baaxo dariifal tan weeqaytitteey,kalwaa kee daroori muhurwah arooca kee lee elle xinta arooca tenek ta aroocah xoqoysimiyya dacrise wayiyyi sabbatah gibdaabini ken yaafeemik dariifa caalat elle aninnaanih gurral madqa abbootan akah teceeh tan xagar yayyaaquwa madqak ugutak dudda le kalali xexxar cabaanamih dirki keenil tan

D.Raymi addat geytitah tan ikoytiini aroocal ginnimtah tan ossotinah weeqi lee tenek too leelwa geeri cuggaanê buqreeral gibdaabina kataasamak gersi kabuki tamaate leelwa tabaatabisak gaba abteh tan hinnay giinook caxitta baayurwat akah caxitannah abaanamih dirki keenil tan

3/ አንድን ውስን ሥራ በክፍያ ወይም ያለክፍያ ለማከናወን ከተለያዩ አካላት ጋር ሊዋዋል ይችላል።

**<u>ክፍል አራት</u>**

**<u>የማህበረሰብ ተፋሰስ ጥበቃ፣አስተዳደርና አጠቃቀም</u>**

**21. <u>የተፋሰስ ልማት ሥራዎች አጠባበቅ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም</u>**

1/ የገጠር መሬት ባለይዞታ መብቶችና ግዴታዎችን አስመልክቶ የሌሎች ሕጎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም በተፋሰስ ውስጥ የሚገኝ የግል ወይም የወል ባለይዞታ እንደ መሬቱ ተፈጥሯዊ አቀማመጥ የአፈርና ውኃ መጠበቂያ ሥራዎችን በመሥራትና በመንከባከብ እንዲሁም በመጠገን የአፈር ክለትን በመከላከል የአፈርን ለምነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።

2/ ማንኛውም የግል ወይም የወል ባለይዞታ
ሀ) በተፋሰሱ ውስጥ በተሠሩ የልማት ሥራዎች ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ልቅ የእንስሳት ስምሪትን የመቆጣጠርና የመጠበቅ ኃላፊነት አለበት፤

ለ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙት የመሬት ይዞታዎቹ ዳር ድንበር፣ በማሳው ውስጥና በመንገዶች ዳር የደን፣ የመኖ ዛፎችንና አልሚ የእፅዋት ዝርያዎችን በመትከል፣ በመንከባከብና በመጠበቅ የአካባቢውን ለምነትና ንነት የመጠበቅ ግዴታ አለበት፤

ሐ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የይዞታ መሬቶቹ አካባቢ ወንዞች፣ ሐይቆች ምንጮች፣ በረቦር ስፍራዎችና ውኃ አዘል መሬቶች ያሉ እንደሆነ እነዚሁ በአጠቃቀምና በአያያዝ ሣቢያ ጉዳት እንዳይደርስባቸው እንደ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው አካል በሚያወጣው ሕግ መሠረት በቂ የመከላከያ የመተው ግዴታ አለበት፣ ርቀት

መ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኘው ይዞታው ላይ የሚፈጠር ትርፍ የጎርፍ ውኃ ቢያጋጥም ይኸው በሌሎች አጎራባች ማሳዎች ላይ ጉዳት እንዳያስከትል፣ ከሌሎች የሚመጣውንም በማቀባበል ወደ ሰው ሠራሽ ወይም የተፈጥሮ መፋሰሻ ቦዮች እንዲፋሰስ የማድረግ ግዴታ አለበት፤

E.Raymi rakaakayal geytima ikoyta le mari ta masayyak lani maasayyak [2][d] keenil radda dirkik yawqoonuh caddook daga yakkeh yan taqabi keenit boode kaa tekkek taham wagsiisah yan gino gaddih dabsimaa kee egla yaysixxigeenim keenil tan

F.Raymi addat geytimtah tan ikoytiini baaxoh addat hinnay maadittel daddoosen hinnammay daddoosanah yanin garboo caxah samaditteey silaalo kee reebitteh sabbatah cuggaaneh yan numih dorba murtii kee kalah leh yan garwa biyaakam takkem mafaxximta

G. Raymi addat wagitah yan xagar faataciseh yan baaxo xoqoysimih ikraaro tanikaa tekkek baaxo ikraarot daddosaanam kee hanaawisaanamih dirki keenil tan

H. Raymi addal girah cararow ugute waaggidah takkaawim maaqatta beyaanamih dirki keenil tan

I. Darba dacrisaanaggidih yagdubeenih yanin taamaaksah gandaado raymih addat geytimta xageega kee dariifal geytimtah yan dubaalaa kee kimbirwa samad dariifa cabba heenih dabboh gexaanamak takkaawimaanamih dirki keenil tan

J.Raymi addat geytimta ikoytiini baaxooxah addat daabissaay hanaawisak yeynebeh yanih yan garboh cooxuuy,qalafta kee aynabeh meqe caxah samadih xaqoysimiyya wagsiisak garbô daddoosuuy dacayri kee xaqoysim madqa kee makko le gurral kalah faxximta madqooqi rakiibo abinal assam faxximta

**22 <u>Bocooy boco akke sinni caxa xalittee kee qaysô xoqoysimiyya</u>**

1. Raymi addat cankah hinnay agleh ikoytittet xoqoysimaanamih gar leh tan maritte ta ikoytittel daddooseenih yanin hinnay daabiseenih yanin kafin bocooy, cooxuuy, waaqiixaay, qaysoo kee boco akke sinni garbo xalittet yantifiqeenimih gar lon

2.Ta maasayyak lani maasayyak [1] galab akak xagen ikoytiinu le marak iroh raymi rakaakayih addat geytima akkinnaanih kafin bocooy waaqiixaay, boco akke sinni garbo xalitte hinnay qayso eglah adoytit sittalluk le ikoyta kinniimih sabittih eglah edde xinta rakiibo abak; egla argaquk maqdisak gaaboysak edde xaqoysimaanam duudaanah

ሠ) በተፋሰሱ ክልል ውስጥ የሚገኝ ባለይዞታ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) (መ) የተጣለውን ግዴታ ለመወጣት ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያጋጠመው እንደሆነ ይህንኑ ለሚመለከተው የተፈጥሮ ሃብት ተቋምና ለማህበሩ ማሳወቅ አለበት

ረ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኘው የይዞታ መሬቱ ውስጥ ወይም ዳር ድንበሮች ላይ ያለማቸው ወይም የሚያለማቸው የደንና የእፀዋት ዝርያዎች በጥላቸውና በጠፈጠፋቸው ምክንያት የተጎራባቹን ባለይዞታ የሰብል ምርትና ሌሎች መብቶች የሚጎዳ መሆን የለበትም፤

ሰ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚመለከተው አካል የፀደቀ የመሬት አጠቃቀም ዕቅድ በሚኖርበት ጊዜ መሬቱን በዕቅዱ መሠረት የማልማትና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፤

ሸ ) በተፋሰሱ ውስጥ የእሳት ቃጠሎ እንዳይነሳ አስፈላጊውን የጥንቃቄ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለበት፣

ቀ) ሰብሉን ለመጠበቅ ከሚያከናውኗቸው ተግባራት በስተቀር በማህበረሰብ ተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ ማሳዎቹና በአካባቢው የሚገኙ የዱር እንስሳትና አዕዋፋት አካባቢውን ለቅቀው እንዳይሰደዱ ጥንቃቄ የማድረግ ግዴታ አለበት፣

በ) በተፋሰሱ ውስጥ በሚገኙ የይዞታ መሬቶቹ ውስጥ ተክሎና ተንከባክበ ያሳደጋቸውን የደን ዛፎች የመኖና አልሚ የእፅዋት ዝርያዎች አጠቃቀምን በተመለከተ በደን ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ህግና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህጎች መሰረት ተግባራዊ መደረግ አለበት።

**22. <u>ስለ እንጨት እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች እና ሣር አጠቃቀም</u>**

1/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በግል ወይም በወል ይዞታዎች ላይ የመጠቀም መብት ያላቸው ሰዎች በእነዚህ ይዞታዎች ላይ ያለሙትን ወይም የተተከለትን ደረቅ እንጨት፣ ዛፍ፣ ቁጥቋጦ ሣር እና እንጨት ያልሆኑ የደን ውጤቶች የመጠቀም መብት አላቸው።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተጠቀሱት ባለይዞታዎች ውጭ በተፋሰስ ክልል ውስጥ የሚገኝ ማናቸውም ደረቅ እንጨት፣ ዛፍ፣ ቁጥቋጦ እንጨት ያልሆነ የደን ውጤት ወይም ግር የማኅበሩ አባላት የጋራ ንብረት ስለሆነ፣ በማኅበሩ ውስጠ ደንብ መሠረት ማኅበሩ ቆርጦ፣ አጭዶና ሰብስቦ መጠቀም ይችላል።

3.Ta maasayyak lani maasayyak[1] kee [2] yal galab akak xagen gadditteh xoqoysimiyyi xayyoyso sarrimaane leh yang gital elle dacrisoonu duudan makkol yagdubeenim faxximta

**23 <u>Raymi rakaakayih addal geytimah yan xeet kee ballaaqe xaqoysimi</u>**

Maqaadin taamoomih kukta rakiibo abak naharal maqaadin amrutiyyi taamal sugteh tan xagoorah gar dirki elle taninnal anuk

1.Ta kuktak maasayyak 25[1] galab akak xagen ikoytiini aroocal geytimta ballaaqe kee xeeti dacrisaanam kee edde xaqoysimaanamih masquuliyyat gar makko le gurral maqaadin taamoomah madqa kekes abak ikoytiinuh leh yan marihim akkele

2.Taymi rakaakayih addat geytimaah agleh lon hinnay doolat ikoytiinut yan aracal geytima xeet ballaaqe makko gurral maqaadin tamoomih madqa rakiibo abak xeet kee ballaaqe raymi daddosu edde yantifiqem duudah

3.Ta maasayyak lani maasayyak [1] [2] maqammudooda tanay immay xeet kee ballaaqe xayyos sarrimaane le gital edde xoqoysimoonu kee dacrisaanam duudoonuh xarriiti corriimiyya kee dariifô biyak kataasamak takkaawimaanam faxximta

**24.<u>Gandaado raymih rakaakayih addat getimta lee gaddat elle xoqoysiman gurra</u>**

Gandaadô raymih rakaakayih addat geytimah yan lee gaddih xoqoysimiyyi makko leh yan lee gaddih xiinissoh madqa elle idnissa gurral abinal asele

**25 <u>nawaacih</u> <u>siirat ayfaafayih mekla</u>**

1.Gandaado raymi daddoosaanamih sababal tantifiqe tan xagowaa gandaado raymih daddoosih siirat nawaacih ayfaafal ofya mekelaanamih dirki keenil tan

2.Ta maasayyak lani maasayyak [1] yal madqam mudo rakiibo abak mekkeltintah tan leet fantaxaw le siirat nawaacih ayfaafay ofya lee gaddih xiinissoh madqa rakiibo abak tanguddubem akkele

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሱት ሀብቶች አጠቃቀም አቅርቦቱን ዘላቂነት ባለው መንገድ ለመጠበቅ በሚያስችል አግባብ መፈፀም ይኖርበታል

**<u>23)በተፋሰሱ ክልል ውስጥ ስለሚገኝ ድንጋይና አሸዋ አጠቃቀም</u>**

በማዕድን ሥራዎች አዋጅ መሠረት ቀድሞ ማዕድን በማምረት ሥራ ላይ የተሰማሩ አካላት መብትና ግዴታ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 25(1) በተጠቀሱት ይዞታዎች ላይ የሚገኙት አሸዋ እና ድንጋይ የመጠበቅ እና የመጠቀም ኃላፊነት እና መብት አግባብነት ባለው የማዕድን ሥራዎች ህግ መሰረት የባለይዞታዎች ይሆናል፤

2. በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በታቀፈና የወል ወይም የመንግሥት ይዞታ በሆነ ሥፍራ ላይ የሚገኝ ድንጋይና አሸዋ አግባብነት ባለው የማዕድን ሥራዎች ህግ መሠረት ድንጋይና አሸዋውን ለተፋሰሱ ልማት ሊጠቀሙበት ይችላሉ፤

3/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች ቢኖሩም የድንጋይና ኣሸዋ አቅርቦቱን ዘለቄታዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀምና ለመጠበቅ እንዲቻል የአፈር ክለትና የአካባቢ መጎዳት እንዳያስከትል ጥንቃቄ መደረግ ይኖርበታል።

**24. <u>በማህበረሰብ ተፋሰሱ ክልል ውስጥ ስለሚገኝ የውሃ ሀብት አጠቃቀም</u>**

በማህበረሰብ ተፋሰስ ክልል ውስጥ የሚገኘውን የውሃ ሃብት አጠቃቀም አግባብነት ያለው የውሃ ሃብት አስተዳደር ህግ በሚፈቅደው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል::

**25<u>. ስለ ሥርዓተ ምሕዳር አገልግሎት ክፍያ</u>**

1/የማህበረሰብ ተፋሰሱ በመልማቱ ምክንያት ተጠቃሚ የሆኑ አካላት ለማህበረሰቡ የተፋሰስ ልማት የሥርዓተ-ምህዳር አገልግሎት ክፍያ የመክፈል ግዴታ አለባቸው።

2/በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ድንጋጌ መሠረት የሚከፈል ከውሃ ጋር የተያያዘ የሥርዓተ ምህዳር አገልግሎት ክፍያ በውሃ ሀብት አስተዳደር ሕግ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል

**26. nawaacih siirat dufih maruuso**

Rakiibô daddoosih xisne hinnammay kali sababah akinnaanih gurral raymal hinnamay raymat xoqoysimal taqabi katasse xagoora tenek kataasen taqabi makko leh tan madqa rakiibo abak qeedalsimtah tan maruuso mekelaanah dariifah qeedalsimah yan nawaaci wag fanah yaydureenih dirki keenil tan

## Konoyhaytoh exxa

## Raymi gandaado wagitta kali caagida

**27 Gaba kalte rami tamoomih attal tabsu**

1.Akinnaanih cankah hinnay kaadu agleh ikoytiinu le num isih ayyuntat,eglat,hinnammay taamak gaba kalla heenih edde tabisan doolat hinnammay doolat akke sinni missoynaani abniseenih yanin raymi daddoosih taamoomi lowwa heenih hirgaanam keenil tan

2.sittal tabsa gexsiisan waqdi tekkeh tan daddos taamoomi mexxat akak daccarsimeh yanim kinnim wagittah yan daqar dabsima diggosam faxximta

**28 elsiisenta wagsissam**

1.Raymi dariifah addat cankah takku agleh takku tekkeh tan taamoomi xarriita kee lee daddoosih dacayrih taamoomi qedebak, makko le gurral hanaawisak raymi addat giffo le xalu bahteh tan ikoytiinu le marah mamaxxaga kee elsiisiyyi elle tamcawwuwayta siirat daqar makkisele

2.Daqar addal tanih tan eglaalik tayseh tan raymi daddoosih taama giffo le taama abteh tan eglah daqar mamaxxagaa kee elsiisenti kaado elle tamcawwu wayta siirat makkisele

**29 nado siirat kee baxsa le hangi faxxah tan ayyunti exxaaxi wagsissa**

1 Akkinnaanih raymi xiinissoo kee mantafaqat gexsot qeedalsimta nadoh inki gide akkiyyi yanim faxximta

2.sayyo kee baxsa le hangi faxah yan exxaaxih xaqoysi geysissa akkinnaanih raymi daddoosih abinittek inkih ligdoo kee mihrat idnisa caddol inki gid yakki gabah assagolla kee xaqoysima yakkeenimih gar keenih amcawwele

**26. የሥርዓተ ምሕዳር ጉዳት ካሣ**

በመሠረተ ልማት ግንባታ ወይም በሌላ ምክንያት በማንኛውም ሁኔታ በተፋሰሱ ወይም በተፋሰስ ተጠቃሚዎች ላይ ጉዳት ያደረሱ አካላት ላደረሱት ጉዳት አግባብነት ባለው ህግ መሰረት ተመጣጣኝ ካሣ መክፈልና አካባቢውን ተመጣጣኝ ወደ ሆነ ሥነ-ምህዳር የመመለስ ግዴታ አለባቸው።

## ክፍል አምስት

## የተፋሰስ ማኅበረሰቡን የሚመለከቱ ሌሎች ጉዳዮች

**27 የተጠናቀቁ የተፋሰስ ሥራዎች ርክክብ**

1 /ማንኛውም የግል ወይም የወል ባለይዞታ በራሱ በኅብረተሰቡ፣ በማኅበሩ ወይም ሥራውን አጠናቅቀው በሚያስረክቡ መንግሥታዊ ወይም መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች የተከናወኑትን የተፋሰስ ልማት ሥራዎች ቆጥሮ መረከብ አለበት።

2/ ርክክብ ሲካሄድ የተሠሩ የልማት ሥራዎች ጥራታቸው የተጠበቀ ስለመሆኑ የሚመለከተው የወረዳ ተቋም ማረጋገጥ አለበት።

**28. ስለማበረታቻ**

1/ በተፋሰሱ ክልል ውስጥ በግልም ሆነ በወል የተሠሩ የአፈርና ውኃ ልማትና ጥበቃ ሥራዎችን እየጠገነ በአግባቡ በመንከባከብ በተፋሰስ ውስጥ የላቀ ውጤት ላስመዘገበ ባለይዞታ የዕውቅና እና ማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ወረዳው ይዘረጋል።

2/ በወረዳው ውስጥ ካሉት ማኅበራት የተሻለ የተፋሰስ ልማት ሥራ ላከናወነ ማኅበር ወረዳው የዕውቅናና ማበረታቻ ሽልማት የሚሰጥበትን ሥርዓት ይዘረጋል።

**29. ስለ ሥርዓተ-ፆታ እና ልዩ ትከረት የሚሹ | የኅብረተሰብ ክፍሎች**

1/ በማናቸውም የተፋሰስ አስተዳደርና አጠቃቀም ሂደት ሚዛናዊ የፆታ ስብጥር መኖር አለበት።

2/ ሴቶችና ልዩ ትኩረት የሚሹ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጥቅም በሚያስገኙ በማናቸውም የተፋሰሱ ልማት ተግባራት ሁሉ አቅማቸውና ሙያቸው በሚፈቅደው መጠን እኩል የመሣተፍ እና ተጠቃሚ የመሆን መብት ይሰጣቸዋል።

**Lecey haytoh exxa**

**Baxaabaxsa le madqammudooda**

**30.malaak kutbeh buxah mas uuliyyata**

1.Makko leh tan dabsimaami kobaahisakaay,faxximmi iyyah yan mihrat qokol acayuk ta kukta abbinoosaanamih masquuliyyat keenil yan

2.Rakaakayitte kee federal fanal raymi daddosih xiisso kee xaqoysimiyyi oytih tabaatabsi siirat akah fidsimannah abele

**31 Rakaakayitte mas-uuliyyata**

1.Rakaakaywa ta kukta kee kalah raymi xiinisso kee xaqoysimit tannoh eglaali xisnee kee giniyya luk angaaraw leh tan madqooqil cubbi ginaanam kee eglaali xisaanamaay,madqooqi abbinoysaanamih mas uuliyyat keenil rada

2. Ta kukta kee kukta abbinoysoonuh yawqu waah yan edde xinta kattaatak roorsimte abbinoysiyyi miracsenta ayyaaqelon

**32 Buqrê maktabi abinaa kee mas-uuliyyata**

Buqre maktab gandaado raymih daddoosih dacayrii kee xiinisso wagsiisak tahaak gubal galab akak xageenih yanin abinaa kee mas-uuliyyata le .

1.Gandaadô raymih daddos ikraaro massoosiyya qokole le axcuk aben missos fokkaaqak lakal faataciselon

2. Raymi daddosih xiinisso kee xaqoysimiyya koobaahiseleeh miraaciseleeh kattaatele

3.Gandaadô raymih eglah adoytit xaqoysima butta ginak culenta geysissah tan taamoomil akah geytiman innah qokolaah kattaatah lowsiisah.

4. inayta raymal gandaadô raymih baar dariifa elle aninnaan innal baaxok daffeyna rakiibo abak margaqa aceele

5.wagitah yan luula taamah egla xisah yan maktab luk koobahsimak gandaadô raymih xoqoysima luula taamah egla xissah tan makaado akah missowtannah abele

**ክፍል ስድስት**

**ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

**30. የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ኃላፊነት**

1) አግባብነት ያላቸውን ተቋማት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህንን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት።

2) በክልሎችና በፌደራል መካከል የተፋሰስ ልማት አስተዳደርና አጠቃቀም የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል።

**31. የክልሎች ኃላፊነት**

1) ክልሎች ይህንን አዋጅና ሌሎች ከተፋሰስ አስተዳደርና አጠቃቀም እንዲሁም ከማኅበራት አመሠራረትና አደረጃጀት ጋር ግንኙነት ባላቸው ሕጎች ላይ ግንዛቤ የመፍጠርና ማኅበራት እንዲመሠረቱ የመቀስቀስና ሕጎቹን የማስፈፀም ኃላፊነት አለባቸው።

2) ይህንን አዋጅና አዋጁን ለማስፈፀም የሚወጣውን ደንብ ተከትለው ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ ያወጣሉ።

**32. የግብርና ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት**

የግብርና ጽ/ቤት ከማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ጥበቃና አስተዳደር ኣኳያ የተጠቀሱት ተግባርና ኃላፊነቶች አሉት፡ በታች

1/ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ዕቅድ ዝግጅትን ይደግፋል ፣ የተዘጋጁትንም መርምሮ ያጸድቃል።

2/ የተፋሰስ ልማት፣ አስተዳደርና አጠቃቀምን ያስተባብራል፣ ይመራል፣ ይከታተላል፣

3)የማህበረሰብ ተፋሰስ ማህበር አባላት የተጠቃሚዎች ቡድን በመመስረት ገቢ በሚያስገኙ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ ይደግፋል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።

4)የዋና ተፋሰስ እና የማህበረሰብ ተፋሰስን ስፋት እንደ አካባቢው መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥ መሰረት በማድረግ ይወስናል።

5/ ከሚመለከተው የህብረት ሥራ ማህበር አደራጅ መስሪያ ቤት ጋር በመተባበር የማህበረሰብ ተፋሰስ ተጠቃሚዎች ህብረት ሥራ ማህበራት መሥራች ኮሚቴ እንዲደራጅ ያደርጋል።

**33 luula taamah ejensih abinaa kee mas-uuliyyata**

Luula taamah eglaali xisuh abbootan akah yeceen xagarih abinaa kee mas-uuliyyata luula taamah eglah kuktal galab akak xagen inna rakiibo abak akkele.

**34 Baysaa kee digaala wagittaama**

1.Ta kuktih abnisso luk abinat fantaaxaw luk abaanah yanin baatilitte, baatil madqa kee kali madqooqil madqammudumtê digaalooli abbinowtam akkel

2.Ta kuktih addat madqammudumte dirkittek awqe waanam kataasah yan xiinissô digaala rorsime kukta abbinoysoonuh yawqu waa eddexintal argiqimele

**35 Elle tabi madqammudo**

1.Ta kukti yawqek naharal sooliseenih sugen gandaado raymih daddoosih luula taamah egla ta kukti faataciseenimik inki sanatih addat ta kukta rakiibo abak faxxiima massos abeenik lakal gandaado taamah egla akkuk yaysaqarreenim keenil tan

2. Duma suge abinal sooliseenih sugen raymi makaado ta kukti mawqaak ugutak xisoonu waan luula taamah eglah taama selta makaado tet aracat gactah fanah oggol aallele

**36 Edde xinta yayyaaqeenimih abbootana**

Ta kuktih abnisiyyah malookti malah buxa edde xinta ayyaaqele

**37 Abnisso taallu wayta madqooqi wagsisa**

Ta kukta sadda akinnaanih kukti edde xintaay, miracsenta hinnammay qaadah abnisso ta kuktih addat caagiidah bagul abbinoosiyya yaallem maduuda

**38 Ta kukti abanal asuwaa widdiiri**

Ta kukti federal nagaarit xaagi waraakit bicca eyyeh yewqe ayrook abbaxuk abinal asele

**33) የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት**

ህብረት ሥራ ማህበራትን ለማደራጀት ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት በህብረት ሥራ ማህበራት አዋጅ በተቀመጠው መሠረት ይሆናል፡፡

**34. ስለጥፋቶችና ቅጣት**

1/ ከዚህ አዋጅ አተገባበር ጋር በተያያዘ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች በወንጀል ሕጉና በሌሎች ሕጎች የተደነገጉ ቅጣቶች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

2/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተደነገጉ ግዴታዎችን አለመወጣት የሚያስከትሉትን አስተዳደራዊ ቅጣት ዝርዝር አዋጁን ለማስፈጸም በሚወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

**35. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ**

1/ ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋሙ የማህበረሰብ ተፋሰስ ልማት ህብረት ሥራ ማህበራት ይህ አዋጅ በፀደቀ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ በዚህ አዋጅ መሠረት አስፈላጊውን ማስተካከያ በማድረግ የማህበረሰብ ተፋሰስ / ህብረት ሥራ ማህበር ሆነው መመዝገብ አለባቸው፡፡

2/ ቀደም ሲል በነበረው አሠራር የተቋቋመ የተፋሰስ ኮሚቴ የዚህን አዋጅ መውጣት ተከትሎ በሚቋቋመው ህብረት ሥራ ማኅበር ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ እስከሚተካ ድረስ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

**36. ደንብ የማውጣት ሥልጣን**

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ያወጣል፡፡

**37. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች**

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም አዋጅ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

**38. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**Addis ababay ximolik 25 HAYTO 2013 I.L.L**

**Sahle werke zewxe**

**Etiyopiyah federaalih demokraasih**

**repobliikih prezedenti**

**አዲስ አበባ ነሐሴ 25th ቀን 2013 ዓ.ም**

**ሳሕለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**